# ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003ን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ማብራሪያ

1. መግቢያ

1.1 ኢትዮጵያ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ለማረጋገጥ እንዲቻል ሥርዓቱ ስለሚቋቋምበት፣ ስለሚተዳደርበት፣ አሠራሩ ስለሚመራበት እንዲሁም አስፈላጊዉ ቁጥጥርና ክትትል ስለሚካሄድበት ሁኔታ በብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 አዉጥታ ሥራ ላይ አዉላለች።

1.2 አዋጁን መሠረት በማድረግ “አር.ቲ.ጂ.ኤስ.” የተሰኘዉን ትልልቅና ወሳኝ ክፍያዎችን የሚያሳልጠዉንና “ኤ.ሲ.ኤች.” በመባል የሚታወቀዉን አዉቶሜትድ የቼክ ማጣሪያ ሥርዓት አጣምሮ የያዘዉ “ኢ.ኤ.ቲ.ኤስ.” የተባለዉ የኢትዮጵያ አዉቶሜትድ የገንዘብ ማስተላለፊያ ሥርዓት እ.ኤ.አ. በ2011 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተግባራዊ መደረጉን ተከትሎ ትልልቅና ወሳኝ ክፍያዎችን በቅፅበት ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላኛዉ መፈፀም ተችሏል። በዚህም ስርዓት አማካይነት በቀን በአማካይ መጠናቸዉ ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ ከ9,500 በላይ ግብይቶች ይተላለፉባቸዋል። ይህም የክፍያ ሥርዓቱን ቀደም ሲል ከነበረበት ሁኔታ ከመሠረቱ የቀየረ ነዉ ማለት ይቻላል። ከዚህም ሌላ እንደ ደመወዝ ያሉትን ብዛት ያላቸዉን ክፍያዎች በባንክ ሂሳብ በኩል በአንድ ጊዜ ለመክፈል የሚያስችለዉ “ክሬዲት ትራንስፈር” አገልግሎት በቅርቡ ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል።

1.3 ከዚሁ ጎን የክፍያ መሠረተ ልማት በማቅረብ የክፍያ ሥርዓቱ እርስ በርሱ የሚናበብና የሚገናኝ በማድረግ ጥቃቅን ክፍያዎችን፣ የአገር ዉስጥ ጨምሮ የካርድ ክፍያን፣ የሞባይልንና የክፍያ ነቁጥን፣ ብሔራዊ ጌትዌይንና ሌሎችንም አገልግሎቶች ከማሳለጥ አኳያ የአስቻይ ሚና እንዲጫወት ኢትስዊች እንደ ብሔራዊ ስዊች እኤአ በ2011 ተቋቁሞ በ2016 ሥራ መጀመሩ ይታወቃል።

1.4 እስካሁን ኩባንያዉ ኤቲኤም.ን፣ የክፍያ ነቁጥን እና ከግለሰብ ወደ ግለሰብ በሞባይል አማካይነት የሚደረገዉን የገንዘብ ዝዉዉር ተናባቢ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በቀን በአማካይ ዋጋቸዉ ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ ከ60,000 በላይ ግብይቶች በዚሁ ስርዓት አማካይነት ይተላለፉበታል። በተመሳሳይ ሌሎቹን መተግበሪያዎችንና የክፍያ መሳሪያዎችን ተናባቢ ለማድረግ የጀመረዉን ሥራ ኩባንያዉ አጠናክሮ ቀጥሏል።

1.5 ከዚህም ሌላ በአዋጁ መሠረት ሶስት መመሪያዎች ማለትም፡- ‹የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ›፣ ‹የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር› እና ‹በወኪል መሥራት› የተሰኙ መመሪያዎች ወጥተዉ ተግባራዊ ተደርገዋል። እነዚህን መመሪያዎች ተከትሎ እስካሁን ኢትዮ ቴሌኮም የክፍያ መሳሪያ አዉጪ ፈቃድ

በመዉሰድ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን ሌሎች ሶስት ኩባንያዎችም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ወስደዉ ወደ ሥራ ገብተዋል። ሌሎቹም በመግባት ላይ ናቸዉ።

1.6 ከብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅ በተጨማሪ የፋይናንስ ተቋማትን አዋጆች ጭምር እንዲከለሱ በማድረግ በመንግሥት በኩል ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት ማለትም በዲጂታል ዘዴ የክፍያ፣ የሃዋላ እና የመድን አገልግሎት አቅራቢዎች እንደ ፋይናንስ ተቋማት እንዲቀጠሩ የተደረገዉ የሪፎርም ሥራ ለዘርፉ ዕድገት በወሳኝ መልኩ አስተዋፅዖ አድርጓል ለማለት ይቻላል።

1.7 በዚህም መሠረት እስካሁን 6,793 ኤ.ቲ.ኤም ተርሚናል፣ 11,714 የክፍያ ነቁጥ ማሽን ፣ 15.5 ሚሊዮን የሞባይል ባንኪንግ ደንበኞች፣ 3.9 ሚሊዮን የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚዎች፣ 28.76 ሚሊዮን ዴቢት ካርዶች፣ 35.5 ሚሊዮን የሞባይል ገንዘብ ተጠቃሚዎች እና 137,378 ወኪሎች በሥራ ላይ መሆናቸዉን እ.ኤ.አ የማርች 2022 መረጃ ያመለክታል። የግብይት ሂሳብ ቁጥርም በከፍተኛ ደረጃ አድጎ 130.4 ሚሊዮን ደርሷል።

1.8 ምንም እንኳን አገራችን ከላይ እንደተጠቀሰዉ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓትንና ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎትን በተመለከተ አስደማሚ ጅምር ላይ ብትሆንም እጅግ ዘግይታ ከመጀመሯ አንፃር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ (ምናልባትም ከ95 በመቶ በላይ) ጥሬ ገንዘብ የሚጠቀም ሲሆን 45 በመቶ የደረሰዉ የፋይናንስ አካታችነት ምጣኔም ከጎረቤቶቻችንና ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች አንፃር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ የሚባል ነዉ። የፋይናንስ አገልግሎት በተለይም የብድር አገልግሎት ከ5 ሚሊዮን ብዙም ያልዘለለ ሆኖ ተደራሽነቱም አዲስ አበባን ጨምሮ በጥቂት ትልልቅ ከተሞችና ተበዳሪዎች አካባቢ ዉስን ሆኖ ይገኛል።

1.9 በሌላ በኩል ምንም እንኳን ከሁለት ዓመታት በፊት የዉጭ አገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን በፋይናንስ ዘርፍ ሙአለ ንዋያቸዉን እንዲያፈስሱ የተፈቀደላቸዉ ቢሆንም ክፍት ተደርጎ ዘለግ ላለ ጊዜ ከቆየዉ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ በስተቀር ዘርፉ ለዉጭ ዜጎች ለበርካታ ዓመታት ዝግ ሆኖ ቆይቷል።

1.10 አገራችን ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2025 የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ዓለምአቀፍ የዲጂታል ሥርዓት አካል ለመሆንና አነስተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ ለመሰለፍ በቁርጠኝነት በመሥራት ላይ ትገኛለች።

1.11 የዲጂታል 2025 ስትራቴጂ አካል የሆነዉና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ እ.ኤ.አ. ከ2021 እስከ 2024 በኃላፊነት ስሜት በመተግበር ላይ ያለዉ ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ፣ በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀዉና እ.ኤ.አ. ከ2021 እስከ 2025 ሊተገበር የታቀደዉ ሁለተኛዉ የብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ ቦርድ ፀድቆ ለትግበራ ዝግጁ የሆነዉ የብሔራዊ የፋይናንስ ዕዉቀት ስትራቴጂ የአገራችንን የክፍያ ሥርዓት ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና አሁን ካለበት ወደላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለኢኮኖሚዉ ዕድገት፣ለፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትና ለፋይናንስ ተደራሽነት የጎላ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ በፅኑ ይታመናል።

1.12 አገልግሎቱን በማስፋትና በጥራት ረገድ በመሻሻል ላይ ያለዉ የቴሌኮም ኔትዎርክና በሙከራ ደረጃ ላይ ያለዉ የተማከለ የብሔራዊ መታወቂያ ትግበራ አገሪቱ ካሉባት ከፍተኛ የፋይናንስ መሠረተ ልማት ተግዳሮቶች አንፃር ተስፋ ሰጪ እርምጃዎች ተደርገዉ ሊወሰዱ ይችላሉ። ከዚህም ሌላ ዲጂታል ክፍያዎችን በአግባቡ በሚመራ ከባቢያዊ ሁኔታ አገልግሎቱን በዘላቂነትና በኃላፊነት መስጠት ዕድገትን ያፋጥናል፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር አስፈላጊዉን መደላድል ይፈጥራል።

1.13 እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መተግበር ቀደም ሲል ከፋይናንስ አገልግሎት የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመድረስ ያስችላል። በተለይም የፋይናንስ አገልግሎት ለሴቶች፣ በአብዛኛዉ በገጠር አካባቢ ለሚገኙ አርሶና አርብቶ አደሮች እንዲሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ጨምሮ ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን አቅም ይፈጥራል። በጥሬ ገንዘብ መጠቀምን በመተው ወደ ዲጂታል አማራጭ መሄድ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ያግዛል፣ የህዝቦችን  የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል አጋጣሚዎችን ይፈጥራል።

1.14 በጥቅሉ ሲታይ ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ የክፍያ ሥርዓቱን ከማዘመን አንፃር የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ሆኖም አሁን አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ አጭር መግለጫ የተዘጋጀዉ አሁን በሥራ ላይ ያለዉን ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ለምን ማሻሻል እንዳስፈለገና በተደረጉት ዋና ዋና ማሻሻያዎች ላይ ማብራሪያ ለመስጠት እንዲቻል ነዉ።

## 2. <u>አዋጁን ለማሻሻል ያስፈለገባቸዉ ዋና ዋና ምክንያቶችና የማሻሻሉ ሂደት</u>

2.1 አዋጁን ለማሻሻል ያስፈለገበት ዋነኛዉ ምክንያት አገራችን በጀመረችዉ አጠቃላይ አገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ማዕቀፍ ዉስጥ በክፍያ ሥርዓት ዘርፍ አስፈላጊዉን የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ በተለይም የመንግሥትን የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግና የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎችን ተሳትፎ በማስፋት የክፍያ ሥርዓቱን ዉጤታማነት፣ አስተማማኝነት፣ አካታችነትና ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ታስቦ ነዉ።

2.2 ሥራ ላይ ከዋለ ከ10 ዓመታት በላይ ሳይሻሻል የቆየዉ አዋጅ ያልሸፈናቸዉን ሆኖም ገበያዉ አበክሮ የሚፈልጋቸዉንና በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉትን ለዉጦች፣ዕድገቶችና መሻሻሎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከተለያዩ አገሮች የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች፣ ከዓለም አቀፍ መርሆችና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማቀናጀት በአዋጁ ዉስጥ ለማካተትና የቁጥጥር ማዕቀፉንም ለማጠናከር ታስቦ ነዉ።

2.3 የአዋጁ ረቂቅ ማሻሻያ በብሔራዊ ባንክ ቦርድ የታየ ነዉ። ከዚህም በተጨማሪ ከመንግሥትና ከአገር ውስጥ የግል የዘርፉ ተዋናዮች ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል። ከተደረገዉ ምክክር ጠቃሚ ግብዓት ተገኝቷል። በተመሳሳይ መልኩ በዘርፉ ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ካላቸዉ የዓለም ባንክ ባለሙያዎችም ጠቃሚ ግብዓት ተወስዷል።

## 3. <u>በረቂቅ አዋጁ ላይ የተደረጉ ዋና ዋና ማሻሻያዎች</u>

### I. <u>የተሻሻሉ ትርጓሜዎች</u>

3.1 የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በረቂቅ አዋጁ ትርጓሜ ዉስጥ ተሻሽለዉ እንዲካተቱ ተደርገዋል፦

- አሁን በሥራ ላይ ባለዉ አዋጅ ንኡስ አንቀፅ 2(12) ለ‹የፋይናንስ ተቋም› የተሰጠዉ ትርጓሜ የጠለፉ መድን ሰጪን፣ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አዉጪንና የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርን ባካተተ መልኩ በረቂቅ አዋጁ ንኡስ አንቀፅ 2(32) እንዲሻሻል ተደርጓል።

- አሁን በሥራ ላይ ባለዉ አዋጅ ንኡስ አንቀፅ 2(18) ለ‹ኦፕሬተር› የተሰጠዉ ትርጓሜ የክፍያ ትእዛዝን ወይም የመንግስት የዋስትና ሰነዶችን የሚያስተላልፍ፣ የሚያቻችል፣የሚያጣራ፣ የተጣራ የመጨረሻ ተከፋይ ሂሳብን የሚወስን እና የሚያወራርድ ስርዓትን እንዲያቋቁምና እንዲሰራ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ የሰጠውን ሌላ ማንኛውንም ኩባንያ በሚያካትት ሁኔታ በረቂቅ አዋጁ ንኡስ አንቀፅ 2(34) ‹የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር› ተብሎ እንዲሻሻል ተደርጓል።

## II. <u>አዲስ ትርጓሜዎች</u>

3.2 የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች፡-

- አንቀፅ 2(4) ‹የመንግስት ሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት›፣
- አንቀፅ 2(29) ‹የዉጭ አገር ገንዘብ›፣
- አንቀፅ 2(30) ‹ኩባንያ›፣
- አንቀፅ 2(31) ‹ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ›፣
- አንቀፅ 2(33) ‹የዉጭ አገር ዜጋ›፣
- አንቀፅ 2(35) ‹ተቀጥላ›፣
- አንቀፅ 2(36) ‹የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ›፣ እና
- አንቀፅ 2(37) ‹የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ›፣

በአዋጁ ላይ የተደረጉትን ማሻሻያዎች ተከትለዉ በረቂቅ አዋጁ ትርጓሜ ዉስጥ በአዲስ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

## III. <u>የተሻሻሉ ድንጋጌዎች</u>

3.3 የክፍያ ሥርዓቱ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዉ ጉድለት ካለበት ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አንድ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ

አዉጪ ሥራዉን እንዳይሠራ ብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ሊከለክለዉ እንደሚችል በሚገልፅ መልኩ አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 5(4) ድንጋጌ በረቂቅ አዋጁ ተመሳሳይ ንዑስ አንቀፅ ሰፋ ብሎና ተሻሽሎ እንዲደነገግ ተደርጓል።

## IV. <u>አዲስ ድንጋጌዎች</u>

3.4 አሁን በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 4(1)(ለ) ተሰርዞ ለመንግስት ሰነዶች ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ግምጃ ቤትን የማቋቋም፣ ተዛማጅ መመሪያና ዉስጠ ደንብ የማዉጣትና ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮቹንም የመመዝገብ ብቸኛ ሥልጣን የብሔራዊ ባንክ እንደሆነ በረቂቅ አዋጁ ተመሳሳይ ንኡስ አንቀፅ በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.5 አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ ንኡስ አንቀፅ 4(2)(ሀ) ተሰርዞ ለክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር እና ለክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ፈቃድ ወይም ይሁንታ የመስጠት ሥልጣን የብሔራዊ ባንክ እንደሆነ በይበልጥ ገላጭ በሆነ መልኩ በረቂቅ አዋጁ በተመሳሳይ ንኡስ አንቀፅ በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.6 አሁን በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 4(2)(መ) ተሰርዞ ተሳታፊዎች፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጭዎችና የክፍያ ስርዓት ኦኘሬተሮች የሥርዓቱን መሠረተ ልማት ግንባታና ተናባቢነት የሚመለከቱ ኢንቨስትመንቶችንና ወጪዎችን ስለሚጋሩበት ሁኔታ፣ ስለሚያስከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ መጠን እንዲሁም ከኤሌክትሮኒክ ሂሳብና ግብይት እንዲሁም ከወኪልና ከሌላ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በጥሬ ገንዘብ ወጪ ከማድረግ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ጣሪያዎችን የመወሰን ሥልጣን ብሔራዊ ባንክ እንደሚኖረዉ በረቂቅ አዋጁ በተመሳሳይ ንኡስ አንቀፅ በአዲስ መልክና በተብራራ ሁኔታ ተደንግጓል።

3.7 አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ አንቀፅ 5 አደዲስና ነባር ንዑስ አንቀፆችን በማካተት ተሻሽሏል። የአዋጁ ንዑስ አንቀጽ 5(1) ተሰርዞ ከብሔራዊ ባንክ በስተቀር ሌላ ማንኛውም ሰው ከባንኩ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር መሆን እንደማይችል በረቂቅ አዋጁ ተመሳሳይ ንዑስ አንቀፅ በተብራራ ሁኔታ በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.8 ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የፅሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በቀር ማንኛዉም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ አዲስ የክፍያ ስርዓት መዘርጋት ወይም አዲስ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ ማዉጣት፣ ከሌላ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ጋር

መቀላቀል ወይም የሌላ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተርን ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪን ሥራ በባለቤትነት መያዝ፣ በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተሩን ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪዉን መሸጥ ወይም የባለሀብትነት መተላለፍ የሚያስከትሉ ማናቸዉንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ዉሎች ማድረግ ወይም የተፈቀደለትን የሥራ ዓይነት መቀየር፣ ራሱ ያወጣዉን አክሲዮን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሳራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ካፒታሉን መቀነስ፣ የመመስረቻ ፅሁፉን ማሻሻል ወይም ሥራዉን እንዲያካሂድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር እንደማይችል በረቂቅ አዋጁ ንዑስ አንቀጽ 5(3) በተዘረዘረና በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.9 የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር በማንኛዉም ጊዜ አግባብነት ያላቸዉን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኛን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ የሀገሪቱን ህጎች ማክበርና መተግበር እንደሚኖርበት በረቂቅ አዋጁ ንዑስ አንቀጽ 5(5) በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.10 አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ አንቀፅ 6 አደዲስና ነባር ንዑስ አንቀፆችን በማካተት ተሻሽሏል። የአዋጁ ንዑስ አንቀጽ 6(1) ተሰርዞ የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ እንዳለበት በሚጠይቅ አግባብ በአዲስ መልክ በረቂቅ አዋጁ ተመሳሳይ ንዑስ አንቀፅ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.11 ባንክ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ ለማዉጣት የብሔራዊ ባንክን ይሁንታ ማግኘት እንዳለበት፣ ከፋይናንስ ተቋምና ከመንግሥት ድርጅት ዉጭ በክፍያ ስርዓት ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛዉም የንግድ ማህበር ተቀጥላ ወይም ራሱን የቻለ ኩባንያ ማቋቋም እንደሚያስፈልግ፣ የመንግሥት ድርጅት በክፍያ ስርዓት ዘርፍ እንዲሰማራ በልዩ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ሊፈቀድ እንደሚገባዉ፣ የዉጭ አገር ዜጎች በክፍያ ሥርዓት ዘርፍ በዉጭ አገር ገንዘብ ሙሉ ንዋያቸዉን ሊያፈስሱ ወይም ተቀጥላ ሊያቋቁሙ እንደሚችሉ፣ ለስትራቴጂክ ድርጅቶች ማለትም ለቴሌኮም ኦፕሬተር፣ ለክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪና ለክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ተጨማሪ ዕድል ለመስጠትና ለቁጥጥር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ተቀጥላ ኩባንያ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ እንዲሁም በክፍያ ስርዓት ዘርፍ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚያስፈልገዉ ዝቅተኛዉ የተከፈለ ካፒታል መጠንና በዘርፉ ፈቃድ ያለዉ የዉጭ ድርጅት የዉጭ ዜጋ ስለሚቀጥርበትና የዉጭ አገልግሎት ሰጪን ስለሚጠቀምበት እንዲሁም ተቀጥላ ከእናት ኩባንያ ጋር ስለሚኖረዉ ግንኙነት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደሚወሰን በረቂቅ አዋጁ ከንዑስ አንቀፅ 6(2) እስከ 6(10) በአዲስ መልክ በዝርዝር ተደንግጓል።

3.12 አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 6(2) በተለይም እንግሊዝኛዉ ትርጉም በ‹ይሁንታ› ላይ ብቻ ያተኮረ ስለሆነ ተሰርዞ የሥራ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰነውን ክፍያ መክፈል እንዳለበት በረቂቅ አዋጁ ንዑስ አንቀፅ 6(11) የ‹ሥራ ፈቃድ›ን ጭምር በሚያካትት መልኩ በአዲስ መልክ እንዲደነገግ ተደርጓል።

3.13 በውጭ አገር ዜጎች የተያዘ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር የኢትዮጵያን ገበያ ሲቀላቀል ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ከለላ ክፍያ ሊያስከፍል እንደሚችል በረቂቅ አዋጁ ንዑስ አንቀፅ 6(12) በአዲስ መልክ ተደንግጓል።

3.14 ለክፍያ ስርዓት ኦፕሬተር ወይም ለክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አዉጪ ይሁንታ ወይም ፈቃድ ለመስጠት በብሔራዊ ባንክ መታየት ያለባቸዉ ጉዳዮች በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 6(14) በአዲስ መልክ በዝርዝር እንዲመላከቱ ተደርገዋል።

3.15 አሁን በሥራ ላይ ያለዉ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 6(6) በተለይም እንግሊዝኛዉ ትርጉም በ‹ይሁንታ› ላይ ብቻ ስለሚያተኩር ተሰርዞ የብሔራዊ ባንክን ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው ማቅረብ ያለበትን አስፈላጊ መረጃዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ባንኩ በሚያወጣዉ መመሪያ ሊወስን እንደሚችል በረቂቅ አዋጁ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6(16) እንዲተካ ተደርጓል።

3.16 ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚደነግጋቸዉ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ-ሁኔታዎች መሠረት ባንኩ በጽሑፍ ሲያጸድቅለት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ኦቨርድራፍትን ጨምሮ አነስተኛ ብድር፣ አነስተኛ ቁጠባ፣ አነስተኛ መድን እና/ወይም ወደ ሀገር የሚላክ ዓለም አቀፍ ሃዋላ ወይም ተዛማጅ አገልግሎት እንዲሰጥ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ከሰጠዉ የፋይናንስ ተቋም ጋር በመጣመር አገልግሎቶቹን በዲጂታል ዘዴ ማሳለጥ እንደሚችል በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 32 በአዲስ መልክ ተደንግጓል።

3.17 ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎችን ለማስተላለፍ፣ ለማጣራት፣ ለመክፈል፣ ለመሳተፍና ለማስተዳደር በሚያስችል የኦፐሬሽን ወይም የስርዓት መዋቅር የሥራ ዘርፍ ለመሠማራት የብሔራዊ ባንክ ይሁንታ እንደሚያስፈልግ በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 33 በአዲስ መልክ ተደንግጓል።

3.18 በክፍያ ስርዓቱ ላይ የተቀናጀ ክትትል በማድረግ የብሔራዊ ክፍያ ስርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ብሔራዊ ባንክ ከአገራዊ፣ ከቀጠናዊና ከዓለም-አቀፋዊ የክፍያ ስርዓት ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ስለሚተባበርበት፣ በጋራ ስለሚሠራበትና ምስጢርን በጠበቀ መልኩ መረጃን ስለሚለዋወጥበት ሁኔታ በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 34 በአዲስ መልክ ተደንግጓል።

3.19 የብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱን ደህንነት፣ውጤታማነትና አስተማማኝነት ለማሳደግ ተገቢነት ያላቸዉን ዓለም-አቀፍ መርሆችና እስታንዳርዶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የራሱ አድርጎ ሊደነግጋቸዉ እንደሚችል በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 35 በአዲስ መልክ ተደንግጓል።